## መግቢያ

መንግስትሰፌመሰረትያለውፈጣን፣ቀጣይነትናፍትሃዊነቱ የተረጋገጠየኢኮኖሚ እድገትበማስመዝገብልማትንየማፋጠንናድህነትንየማስወገድዓላማያለውሲሆን ባለፉትዓመታትየአገሪቱን አጠቃላይየኢኮኖሚ እንቅስቃሴለመምራትየሚያስችል የረጅምናየመካከለኛዘመንየልማት እቅድ ተዘጋጅቶ በመተግበር ላይ ነው፡፡

በሀገር ደረጃ የተነደፉ የልማት እቅዶችን ለመተግበር በሁሉምደረጃየሚያስፈልገውን የማስፈፀም አቅምማሳደግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ትምህርትን በየደረጃው ማስፋፋትና ጥራቱን ማረጋገጥ የግድ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በትምህርቱ ዘርፍ የቅድሚያ ትኩረት ከተሰጣቸው ዘርፎች አንዱ አጠቃላይ ትምህርት ነው፡፡ ስለሆነም በ1986 ዓ.ም የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ በመቅረፅ እና ፖሊሲውን ስራ ላይ ለማዋል ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ በተነደፉ/በተዘጋጁት ተከታታይ የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራሞች የትምህርት ተደራሽነትን፣ፍትሀዊነትን እና አግባብነትን በየደረጃው ከማሳደግ አኳያ አበረታች ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡

ትምህርትን ከማስፋፋት ጎን ለጎን ጥራቱን ለማረጋገጥ የሚረዱ ስልቶችን በመንደፍ በትምህርት ቤቶች ለመማር ማስተማሩ አጋዥ የሆኑትን የትምህርት ግብዓት፣ ሂደትና ውጤት በማሻሻል የተማሪዎችን እውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ለማጎልበት በ1999 ዓ.ም የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፓኬጅ ተቀርፆ በሁሉም የሀገራችን ክልሎች በመተግበር ላይ ነው፡፡ ፓኬጁ የመምህራን ልማት፤ የሥርዓተ ትምህርት፣ መጻህፍትና ምዘና፤ የትምህርት ቤት መሻሻል፣ የትምህርት አመራርና አስተዳደር፤ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ እንዲሁም የሥነ ዜጋና ሥነ ምግባር መርሀ ግብሮችን አካቷል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በሁሉም የአገሪቱ ክልሎች በሚገኙ ትምህርት ቤቶች የመርሀ ግብሮቹን አፈጻጸም ለመገምገም የሚያስችል የኢንስፔክሽን ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኗል፡፡

አለም አቀፍ ተሞክሮዎች እንደሚያሳዩት በትምህርት ቤቶች የሚካሄድ ተከታታይ ኢንስፔክሽን የተማሪዎችን ውጤት ለማሻሻልና የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡ የኢንስፔክሽን የግምገማ ውጤት የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፓኬጅ በተለይም ደግሞ የትምህርት ቤት ማሻሻያ መርሀ ግብር አተገባበርን በተመለከተ መረጃ የሚሰጥ ሲሆን በዚህም ትምህርት ቤቶች ቀዳሚ የትኩረት ጉዳዮችን

ለመለየት እንዲረዳቸው የሚያካሂዱት ግለ-ግምገማ ተገቢውን ሂደት የተከተለ መሆኑን ለመፈተሽና የማሻሻያ ሃሳቦችን ለመጠቀም የበኩሉን ድርሻ ያበረክታል፡፡

ትምህርት ሚኒስቴር የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ በመንግስት የተሰጠውን ሃላፊነት መሰረት በማድረግ በ2004 ዓ.ም የአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬትን ያቋቋመ ሲሆን የዚህ የስራ ክፍል ሃላፊነት ከክልል/ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮዎች፤ በነሱም በኩል ከዞን/ክፍለ ከተማ ትምህርት መምሪያዎችና ከወረዳ ትምህርት ጽ/ቤቶች ጋር በመተባበር በሁሉም የሀገሪቱ ክልሎች በአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ በየደረጃው በሚገኙ ትምህርት ቤቶች የኢንስፔክሽን ስራ ለማከናወን የሚረዳ ሥርዓት መዘርጋት፣ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት እንደ አስፈላጊነቱ ሙሉ፣ ከፊል፣ ተከታታይና የተወሰነ ጉዳይ ላይ ያተኮረ የኢንስፔክሽን ስራ ሊያካሂድ ይችላል፡፡

በዚሁ መሠረት ትምህርት ሚኒስቴር ት/ቤቶች ያሉበትን የአፈጻጸም ደረጃ ከግብዓት፣ ከሂደትና ውጤት አኳያ ለመመዘን የሚያስችል ሀገር አቀፍ የኢንስፔክሽን ማዕቀፍ ያዘጋጀ ሲሆን ማዕቀፉም በትምህርት ቤቶች ኢንስፔክሽን በምን መልክ መካሄድ እንዳለበት አጠቃላይ ሁኔታዎችን ሲያመለክት፤ይህ ሀገር አቀፍ የትምህርት ቤቶች ኢንስፔክሽን መመሪያ የማዕቀፉ ማሟያ ከመሆኑ በተጨማሪ በውስጡ የኢንስፔክሽን ሂደት፣ የአፈጻጸም ስልቶች፣ ከፌዴራል ትምህርት ሚኒስቴር እስከ ት/ቤት ድረስ ያሉ አካላት ሃላፊነትና የሥራ ድርሻ እንዲሁም የኢንስፔክተሮች ሙያዊ ስነምግባርን በውስጡ አካቶ ይዟል፡፡

# ክፍልአንድ
# ጠቅላላ

## 1 አጭርርዕስ

ይህ መመሪያ የትምህርት ሚኒስቴር ሀገር አቀፍ የአጠ/ትም/ኢንስፔክሽን አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 82/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2 አውጭውባለስልጣን

የትምህርት ሚኒስቴር የአስፈጻሚ አካላትን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 በተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት መሠረት ይህን የአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን የአፈጻጸም መመሪያ አውጥቷል፡፡

## 3 ትርጓሜ

በዚህ የአፈፃፀም መመሪያ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

3.1 “ኢንስፔክሽን” ማለት” - በአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ የትምህርትጥራትን ለማስጠበቅ የሚያስችል የተቋማትግምገማ በማካሄድክትትልና ድጋፍየሚያደርግና የተጠያቂነት ስርዓትን የሚያሰፍንየሥራ ዘርፍ ነው፡፡

3.2 ”ግብዓት” ማለት - በትምህርት ተቋማት ለመማር ማስተማር ሂደትአስፈላጊ የሆኑ የሰው፣ የገንዘብናየቁሳቁስ…ወዘተ ሀብትን የሚመለከት ነው፡፡

3.3 ”ሒደት” ማለት - በትምህርት ተቋማት ውስጥ የተማሪዎችን ውጤትና ስነምግባር ለማሻሻል የሚከናወንተግባር ነው ፡፡

3.4 ”ውጤት ” ማለት በመማር ማስተማር ሂደትና በዕለት ከዕለት እንቅስቃሴ መስተጋብር የሚመጣ የተማሪዎችየእውቀት፣ክህሎት እና አመለካከት አወንታዊ ለውጥ ነው፡፡

3.5 "ግለ-ግምገማ" ማለት የትምህርት ተቋማት አፈጻጸማቸውን ወይም ያሉበትን ደረጃ ራሳቸውን በራሳቸውየሚያዩበት አግባብ ማለት ነው፡፡

3.6 "የትምህርት ቤቶች ደረጃ ምደባ" ማለት ትምህርት ቤቶችን ከግብዐት፣ ከሂደትና ከውጤት አኳያ በተቀመጡ ስታንዳርዶችና አመልካቾች መሠረትበመለካት ደረጃ የመስጠት ተግባር ነው፡፡

3.7 "የትኩረት መስኮች" ማለት የትምህርት ኢንስፔክሽን በዋናነት የሚያተኩርባቸው ርዕሰ ጉዳዮች ማለት ነው፡፡

3.8 "ስታንደርድ" ማለት - ሁሉንም ት/ቤቶች በአንድ አይነት ይዘት ፣ አሰራር ስረዓትና በተገኘ ውጤት ላይ ለመለካት የተቀመጠ መስፈርት ነው፡፡

3.9 "አመልካች " ማለት - ለእያንዳንዱ ስታንዳርድ የመለኪያውን ቁልፍ ባህርይየሚያመለክት ማለት ነው፡፡

# 4 የተፈጻሚነትወሰን

የትምህርት ቤቶች ኢንስፔክሽን መመሪያ በመላው ኢትዮጵያ በሚገኙ የትምህርት ተቋማት ማለትም በአጸደ ሕጻናት ፣ በመጀመሪያ ደረጃ ፣ በአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃና በመሰናዶ ት/ቤቶች ፣ በአማራጭ መሰረታዊ የትምህርት ማዕከላት የመንግስት ፣ የህዝብና የግልና የሌሎች ትምህርት ተቋማት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡የመምህራን ትምህርት ኮሌጆችና የተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት መስጫ ጣቢያዎችን ይህ የኢንስፔክሽን መመሪያ አይመለከታቸውም፡፡

ይህ መመሪያ የት/ቤቶችን የትምህርት ጥራት የማረጋገጥ እንቅስቃሴ ለመገምገም በት/ሚኒስቴር የአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት እንዲሁም በክልል ትምህርት ቢሮዎች፣ በዞን/ክፍለ ከተማ ትምህርት መምሪያዎችና በወረዳ ትምህርት ቤቶች በተቋቋሙ የኢንስፔክሽን የሥራ ዘርፎች ተፈፃሚ ይሆናል።

# 5 የጾታአገላለጽ

በዚህ መመሪያ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸ ቃል ወይም አባባል የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

## 6 የመመሪያውዓላማዎች

የመመሪያው ዋና ዓላማየትምህርት ጥራትንና ውጤታማነትን በማረጋገጥ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተማሪዎችን ውጤትና ሥነምግባር ማሻሻል ሲሆን የሚከተሉትን ዝርዝር ዓላማዎች አካቷል፡-

6.1 ትምህርት ቤቶች የሚጠበቅባቸውን ዝቅተኛ/ ተፈላጊ የአፈጻጸም ደረጃ ማሟላታቸውን ለማረጋገጥ፣

6.2 ት/ቤቶችን በደረጃ መመደብና ሞዴል ት/ቤቶች የጉድኝት ማዕከላት ሆነው ሌሎችን እንዲያበቁ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት፣

6.3 የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፓኬጅ በተለይም የትምህርት ቤት ማሻሻያ መርሃ-ግብርን አተገባበርና ውጤታማነት በመፈተሽ ለፖሊሲ አውጭዎችና ለትምህርት ባለሙያዎች መረጃ ለመስጠት፣

6.4 በትምህርት ጥራት ማረጋገጥ ስራ ትምህርት ቤታቸው ስላለበት ደረጃ ለወላጆች፣ መምህራንና ተማሪዎች መረጃ ለመስጠትና ተሳትፏቸውን ለማጎልበት፣

6.5 ትምህርት ቤቶች ሶስቱን የልማት አቅሞች/ የድርጅት፣ የመንግስትና የህዝብ ክንፎች/ በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ ተጣምረው በትምህርት ተደራሽነት፣ ፍትሃዊነት፣ ብቃት፣ አግባብነትና ጥራት ላይ መረጃ በመስጠት ተሳትፏቸውን በማጎልበት የተማሪዎችን ውጤትና ስነምግባር እንዲያሻሽሉ ለማድረግ፣ የትምህርት ቤቶች መሻሻልና አፈጻጸምን አስመልክቶ በየደረጃው የተጠያቂነት ስርዓት ለማስፈን ነው፡፡

## 7 የኢንስፔክሽንመሪመርሆዎች

የኢንስፔክሽን ሂደት የሚከተሉትን መሠረታዊ መሪ መርሆዎችን ይከተላል፡፡ እነርሱም፡-

7.1ነጻ ወይም የት/ቤቱ አካል ባልሆኑ የትምህርት ኢንስፔክተሮች ይካሄዳል፡፡

7.2የአንድን ትምህርት ቤት አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴ ለመገምገም ተጨባጭ፣ ወጥነትና ቀጣይነት ባላቸው መረጃዎች ላይ ተመስርቶ ይካሄዳል፡፡

7.3ግምገማው ሁሉንም ት/ቤቶች ባካተተ መልኩ በተቀመጡት ግልጽ ስታንዳርዶችና መስፈርቶች መሠረት የሚካሄድ እንጂ የኢንስፔክተሮች ግላዊ አመለካከት መንፀባረቅ የለበትም።

7.4ገንቢ እና ለጉዳዮች ትኩረት የሚሰጥ ፤ የተከናወኑ መልካም ተግባራትን የሚያበረታታና እጥረቶችን ለይቶ በማውጣት የማሻሻያ ሃሳብ የሚሰጥበት ተግባር ነው፡፡

7.5የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ ስብእና በማክበር ይከናወናል፡፡

7.6የግምገማ ተግባራት ት/ቤቶች እንደ ተቋም ባስመዘገቡት ውጤት ላይ ያተኮረ እንጂ በግለሰቦች የሥራ አፈጻጸም ላይ መሆን አይገባውም፡፡

# 8 የመመሪያውአስፈላጊነት

ጥራትን የማረጋገጥ ሂደት ለትምህርት ቤቶች መሻሻል መሠረታዊ ሲሆን ኢንስፔክሽን አንዱ የጥራት ማረጋገጫ ዓይነት ነው፡፡ በትምህርት ቤቶች የሚካሄደው ኢንስፔክሽን የመማር ማስተማር መስተጋብሩ ጥራቱን በጠበቀና የተማሪዎችን ውጤትና ስነ-ምግባር ማሻሻል ላይ ያነጣጠረ እንዲሁም በተጨባጭ መረጃ ላይ የተመሰረተ እና ያልተዛባ ምዘና የሚሰጥበት ተግባር ነው ፡፡

በመሆኑም ሁሉም ትምህርት ቤቶች ሊያሟሉት የሚገባ ዝቅተኛ /ተፈላጊ/ የብቃት ደረጃዎችን በመወሰን ትምህርት ቤቶችን በመልካም አፈጻጸማቸው ለማበረታታት ወይም ላሳዩት ደካማ አፈጻጸም ት/ቤቱና በየደረጃው የሚመለከታቸው አካላት ተጠያቂ የሚሆኑበትን ስርዓት ለመፍጠር የትምህርት ቤት ኢንስፔክሽን አስፈላጊ ነው፡፡

# 9 የአፈጻጸምመመሪያውጥቅሞች፡-

9.1ትምህርት ቤቶች የሚጠበቅባቸውን የአፈጻጸም ደረጃ በግልጽለማሳየት፣

9.2 ትምህርት ቤቶች ችግሮችን በመለየት ለመሻሻልየሚያስፈልጋቸውን ጉዳዮችለመጠቆም፣

9.3 ትምህርት ቤቶች ለመሻሻል ቅድሚያ የሚሰጧቸውን ጉዳዮችመለየትእንዲችሉ ለመርዳት፣

9.4 የኢንስፔክተሮችን ልምድና ሙያ በመጠቀም በኢንስፔክተሮች፣በትምህርት ቤት መምህራን፣ ርዕሳነ መምህራን እናሱፐርቫይዘሮች መካከል የሚደረጉ ገንቢ ውይይቶችን ለማሳለጥ፣

9.5 ትምህርት ቤቶች አፈጻጸማቸውን መገምገም እንዲችሉ ክህሎታቸውን ለማዳበር፣

9.6 በት/ቤቶች መካከል ጤናማ የውድድር መንፈስ ለመፍጠር፣

9.7 በየደረጃው ያሉ አመራር ለት/ቤቶች የሚሰጡትን ድጋፍ ለማመላከት ነው፡፡

# ክፍልሁለት

## 10 የኢንስፔክሽንሂደት

የኢንስፔክሽን የትኩረት መስኮች የትምህርት ቤት አካባቢን፣ የትምህርት ቤቱ አመራርና አስተዳደርን ፣ መማር-ማስተማርን ፣ ከወላጆችና ከህብረተሰቡ ጋር ያለ ግንኙነትን እና የተማሪዎች ውጤትን መሠረት ያደረገ ሲሆን ከግብዓት ፣ ከሂደት እና ከውጤት ጋር የተሳሰሩ ናቸው፡፡ የኢንስፔክሽን ሥራ ለማከናወን የሚከተሉትን ሂደቶች በትኩረት መከተልና መተግበር ይገባል፡፡

## 10.1ቅድመኢንስፔክሽን

### 10.1.1 ለኢንስፔክሽንሥራየትምህርትቤቶችአመራረጥ፡-

በሀገር አቀፍ የኢንስፔክሽን ማዕቀፍ ላይ በግልፅ እንደተቀመጠው የሁሉም ትምህርት ቤቶች ኢንስፔክሽን ቢያንስ በሦስት አመት አንድ ጊዜ ይካሄዳል፡፡ በየዓመቱ

ለሚካሄደው የኢንስፔክሽን ስራ የሚመረጡ ትምህርት ቤቶች በክልል/ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮዎች፣የዞን/ክፍለ ከተማ ትምህርት መምሪያዎችና የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤቶች በሚያደርጉት ምክክር ይሆናል። አመራረጡ የትምህርት ቤቶችን ብዛት፣ ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥና / ገጠር፣ ከተማ/ የትምህርት ቤቶችን የአፈፃፀም ደረጃ ያገናዘበ መሆን ይጠበቅበታል፡፡ የየክልሉ/ከተማ መስተዳድር ትምህርት ቢሮ የተመረጡ ትምህርት ቤቶችን አጠቃላይ መረጃ ለትምህርት ሚኒስቴር ማሳወቅ ይጠበቅበታል፡፡

### 10.1.2 የኢንስፔክሽንቡድንአመሰራረት፡-

የክልል ትምህርት ቢሮ የዞን/የክፍለ ከተማ ትምህርት መምሪያ/ጽ/ቤት እናወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት የኢንስፔክሽን ዘርፍ አንድን ትምህርት ቤት ለመገምገም ቢያንስ ሁለት አባላት ያሉት የኢንስፔክሽን ቡድን ማዋቀር ይጠበቅበታል። የኢንስፔክሽን ቡድኑ በአንድ የትምህርት ተቋም ለሶስት ወይም ለአራት ቀናት ስራዎችን ሲያከናውን ይቆያል፡፡ ከቡድኑ አባላት መካከል አንዱ/አንዷ በአስተባባሪነት ይሰየማል/ትሰየማለች፡፡

### 10.1.3 ከትምህርትቤቶችጋርየሚደረግግንኙነት፡-

የኢንስፔክሽን ስራ የሚከናወንበት ት/ቤት ከሁለት ሳምንት በፊት እንዲያውቁት ይደረጋል፡፡ለኢንስፔክሽን ስራም እንደ ግብዓትነት ሊያገለግሉ የሚችሉ አሰፈላጊ የሆኑ ዋና ዋና መረጃዎችን ት/ቤቱ በሚቀርብለት ጥያቄ መሠረት አስቀድሞ ማቅረብ አለበት፡፡ ት/ቤቱ ያቀረበውን መረጃዎች ኢንስፔክተሮች በአግባቡ ተንትነው በኢንስፔክሽን ወቅት ስራ ላይ ማዋል ይኖርባቸዋል፡፡

### 10.1.4 የት/ቤትደረጃምደባስለማካሄድ፡-

እያንዳንዱ ት/ቤት በሀገር አቀፍ የት/ቤቶች ደረጃ ምደባ ማዕቀፍ መሠረት በትምህርት ዓመቱ መጨረሻ ወይም መጀመሪያ ግለ-ግምገማ በማካሄድ ለትምህርት ቤቱ ደረጃ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡ ኢንስፔክተሮች በኢንስፔክሽን ጊዜ የትምህርት ቤቶቹን ግለ-ግምገማውንና ደረጃ ምደባውን ትክክለኛነት ያረጋግጣሉ፡፡

## 10.2 በኢንስፔክሽንወቅት

### 10.2.1 የኢንስፔክሽንሥራአጀማመር፡-

የኢንስፔክሽን ባለሙያዎች ትምህርት ቤት እንደደረሱ ከትምህርት ቤቱ ር/መምህር/ት እና ሌሎች የትምህርት ቤቱ አመራሮች ጋር በመገናኘት ስለሚያከናዉኑት የኢንስፔክሽን ሥራ ዓላማና አጠቃላይ ሁኔታ ገለፃ ያደርጋሉ፡፡ የትምህርት ቤቱ አመራርየት/ቤቱን ነባራዊ ሁኔታ በተመለከተ አጭር ገለጻ ያቀርባሉ፡፡ ኢንስፔክተሮቹ በኢንስፔክሽን ወቅት በየጊዜው ከትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር/ት ጋር በመገናኘት ከስራው ጋር ተያይዞ የሚነሱ ጥያቄዎች እና ችግሮችን በአፋጣኝ ለመፍታት ጥረት ያደርጋሉ፡፡

### 10.2.2 መረጃአሰባሰብ፡-

ኢንስፔክተሮች ስለ እያንዳንዱ ስታንዳርድ አፈፃፀም ትክክለኛ ውሣኔ ላይ ለመድረስ እንዲያስችላቸው ሙሉ ጊዜያቸውን ትምህርት ቤቱ ውስጥ የተለያዩ መረጃዎችን/ማስረጃዎችን በመሰብሰብ ያሳልፋሉ፡፡የሚሰበሰቡት መረጃዎች/ማስረጃዎች በኢንስፔክሽን ማዕቀፍ ውስጥ የተቀመጡትን ስታንዳርዶች መሠረት በማድረግ መሆን ይኖርበታል፡፡

### 10.2.3 የክፍልውስጥምልከታ

10.2.3.1 ለኢንስፔክሽንስራየተሰማራውቡድንከመማርማስተማርተግባርጋርቀጥተኛግንኙነትያላቸውንተግባራትበትኩረትማከናወንይጠበቅበታል፡፡በአንድጊዜበሁሉምክፍሎችበመገኘትምልከታለማድረግእጅግአስቸጋሪበመሆኑበናሙናነትበተመረጡክፍሎችናየተወሰኑመምህራንንየመማርማስተማርሂደትበመመልከትእንዲሁምበየትምህርትአይነቱስልትበመቀየርስይከናወናል፡፡ቡድኑለሚያከናውናቸውእንቅስቃሴዎችናምልከታዎችበቅድሚያፕሮግራምማስያዝአስፈላጊነው።

10.2.3.2 የክፍል ምልከታው በአንድ ሙሉ የትምህረት ክፍለ ጊዜ /Period/ ይከናወናል፡፡ በመማር ማስተማር ሂደት ወቅት የሚከናወን ምልከታ ጥንቃቄ የሚጠይቅ ሲሆን ኢንስፔክተሩ/ሯ በክፍል ውስጥ የሚያከናውነው/የምታከናውነው ተግባር ሁሉ ሥርዓትና አክብሮት ያልተለየውና የመማር ማስተማር ሂደቱን የማያውክ መሆንአለበት፡፡

### 10.2.4 የኢንስፔክሽንትግበራንበተመለከተክትትልስለማድረግ፡-

**ሀ. የመጀመሪያ ኢንስፔክሽን አገልግሎት አሰጣጥ፡-**

እያንዳንዱ ት/ቤት ቢያንስ በሶስት አመት አንድ ጊዜ በኢንስፔክሽን በውድን መታየት ይኖርበታል፡፡

**ለ. የድጋሚ ኢንስፔክሽን አገልግሎት ሰለማግኘት፡-**

አንድ ትምህርት ቤት ደረጃውን ካላሟላ ከአንድ አመት በኋላ እንደገና በኢንስፔክሽን ይታያል፡፡

## 10.3 ድህረኢንስፔክሽን

## 10.3.1 የተጠቃለለየትምህርትቤቶችየአፈፃፀምምዘናደረጃአሰጣጥ፡-

ኢንስፔክተሮችለየስታንዳርዱ የተቀመጡ አመልካቾችን በመጠቀምና የተሰበሰቡ መረጃዎችን በማጠናቀር የትምህርት ቤቱን የአፈጻጸም ደረጃ የሚያሳይ ትክክለኛ ውሳኔ/ብይን መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡ለእያንዳንዱ ስታንዳርድ የሰጡትን ውሳኔ መሠረት በማድረግ የትምህርት ቤቱን አጠቃላይ ነባራዊ ሁኔታ በአራት የደረጃ መለኪያዎች ይመዝናሉ፡፡መመዘኛዎችም፡-

ሀ. ከ50% በታች ከሆነ ትምህርት ቤቱ ደረጃ 1 ላይ ይመደባል፣

ለ. ከ50% - 69.99% ከሆነትምህርት ቤቱ ደረጃ 2 ላይ ይመደባል፣

ሐ. ከ70% - 89.99% ከሆነትምህርት ቤቱ ደረጃ 3 ላይ ይመደባል፣

መ. ከ90% - 100% ከሆነ ትምህርት ቤቱ ደረጃ 4 ላይ ይመደባል፣

በዚህም መሰረት ኢንስፔክተሮች ሁሉንም ስታንዳርዶች በተቀመጡ አግባቦች መሰረት በመፈተሽ ሙያዊ ውሳኔመስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 10.3.2 የኢንስፔክሽንማጠቃለያሪፖርትአቀራረብ፡-

### 10.3.2.1 የቃልግብረ-መልስ

የኢንስፔክሽን ስራ እንደተጠናቀቀ የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር፣ሱፐርቫይዘርና ሌሎች የሚመለከታቸው አመራር እንዲሰባሰቡ በማድረግ የኢንስፔክሽን ቡድኑ ያስቀመጣቸውን ውሳኔዎች /Judgements/፣ ለትምህርት ቤቱ መሻሻል ጠቃሚ አስተያየቶችበቃል ያቀርባል፡፡ በተጨማሪም በትምህርት ቤቱ ተዘጋጅቶ በሚቀመጥ አስተያየት መስጫ ካርድ ወይም መዝገብ ላይ ዋና ዋና አስተያየቶችን ማስፈር ይገባል፡፡

### 10.3.2.2 የጽሁፍሪፖርትአቀራረብ፡-

ሀ/ ንስፔክሽን ተግባር ከተጠናቀቀ ሁለት ሳምንት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የጽሁፍ ሪፖርት በአግባቡ ተዘጋጅቶ የኢንስፔክሽን አገልግሎት ለተሰጠበት ትምህርት ቤት እና በየደረጃው ኢንስፔክተሮቹ ተጠሪ ለሆኑባቸው ለወረዳው ትምህርት ጽህፈት ቤት፣ ለዞን፣ ለክልሉ ት/ቢሮ ኢንስፔክሽን ዘርፍና ለትምህርት ሚኒስቴር አጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት መቅረብ አለበት፡፡

ለ/ኢንስፔክሽን ሪፖርት አቀራረብ የተመጠነ፣ ግልጽና በመረጃ ላይ ተመስርቶ በጥንቃቄ የተዘጋጀ መሆን ይኖርበታል፡፡

ሐ/ ኢንስፔክሽን ቡድን አባላት በሪፖርት ዝግጅት፣ጥራትና ተገቢነት ላይ የጋራ ሃላፊነት እና ተጠያቂነት አለባቸው፡፡

መ/ኢንስፔክሽን ሪፖርት እንደ አስፈላጊነቱ በድረ-ገጽ /Web site/ አማካኝነት እንዲሰራጭ ይደረጋል፡፡

# ክፍልሶስት

# አደረጃጀት

# 11 በአጠቃላይትምህርትኢንስፔክሽንዘርፍየፈጻሚ/አስፈጻሚአካላት ኃላፊነትናተግባር

## 11.1 በትምህርትሚኒስቴርየአጠቃላይትምህርትኢንስፔክሽንዳይሬክቶሬ ት፡-

11.1.1 ሀገራዊና ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በማድረግ ሀገራዊ የኢንስፔክሽን ማዕቀፍ ፣ መመሪያዎችን የማዘጋጀትና የማሻሻል ሥራዎችን ያከናውናል፡፡

11.1.2 ከክልል/ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮዎች ኢንስፔክሽን ዘርፍ ጋር በመቀናጀት ወይም በተናጠል እንደ አስፈላጊነቱ የኢንስፔክሽን ሥራ ያከናውናል፡፡

11.1.3 ስልጠናዎችን ያዘጋጃል፣ ይሰጣል፤ እንደ አስፈላጊነቱም በየክልሉ ለሚገኙ የኢንስፔክሽን ባለሙያዎች አቅጣጫ አመልካች የሆነ ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

11.1.4 በክልል/ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮዎች ኢንስፔክሽን ዘርፍ ስለሚከናወኑ አመታዊ የኢንስፔክሽን ስራዎች የጋራ ዕቅድ በማዘጋጀት ስምምነት ላይ ይደርሳል፡

11.1.5 ከየክልሉ/ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮዎች ኢንስፔክሽን ዘርፍ የሚከናወኑ የኢንስፔክሽን ሥራዎች በሀገር አቀፉ ማዕቀፍ (Framework) መሠረት እየተከናወነ ስለመሆኑና ወቅታዊ ሪፖርቶች ተዘጋጅተው እንዲላኩ ክትትልና ግምገማ ያደርጋል፡፡

11.1.6 ከየክልሉ የሚላኩ ሪፖርቶችንና ዳይሬክቶሬቱ በመስክ በመገኘት ያጠናቀራቸውን መረጃዎች በማሰባሰብ አመታዊ ሪፖርት ያዘጋጃል፣ ለሚመለከተው አካል ያሰራጫል፡፡

11.1.7 ከሁሉም ክልሎች/ከተማ አስተዳደር ት/ቢሮዎች ኢንስፔክሽን ዘርፍ በየሩብ ዓመቱ ተዘጋጅተው የሚላኩ ሪፖርቶችን በማጠናቀርና በመተንተን የኢንስፔክሽን ተግባር ያስገኘውን ጥቅም ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፡፡

11.1.8 መልካም ተሞክሮዎች በመቀመርና በመለየት እንዲስፋፉ ያደርጋል፡፡

11.1.9 የኢንስፔክሽን መረጃ ይሰብስባል፣ ያደራጃል፣ ይተነትናል፣ ጥቅም ላይ ያውላል፤ ወቅታዊነቱን ይጠብቃል፡፡

11.1.10 በኢንስፔክሽንና በሌሎች የተለያዩ መንገዶች የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ በተከናወኑ ተግባራት ላይ ከአለም አቀፍ ተሞክሮዎች ጋር በማመዛዘን ጥናትና ምርምር ያከናውናል፡፡

## 11.2የክልል/ከተማአስተዳደርትምህርትቢሮኢንስፔክሽንዘርፍ፡-

11.2.1. በሀገር አቀፉ የኢንስፔክሽን ማዕቀፍና መመሪያ መሠረት የኢንስፔክሽን ተግባር ያከናውናል፡፡

11.2.2. የትምህርት ቤቶች ኢንስፔክሽን ተግባር በአመታዊ የዕቅድ መርሃግብር መሠረት መከናወኑን ያረጋግጣል፡፡

11.2.3. የኢንስፔክሽን ሥራዎችን የተመለከተ የየሩብ ዓመት ሪፖርት ለትምህርት ሚኒስቴር ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት በወቅቱ ይልካል፡፡

11.2.4. በክልሉ/ከተማ አስተዳደር ለሚገኙ የዞን/ ክፍለ ከተማ ትምህርት መምሪያና የወረዳ ት/ቤቶች ፅ/ቤት የኢንስፔክሽን ባለሙያዎች ስልጠና ያዘጋጃል፣ ይሰጣል፣ ሙያዊ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

11.2.5. በዞን/ ክፍለ ከተማ ትምህርት መምሪያና በወረዳ ትምህርት ፅ/ቤት ደረጃ የሚከናወኑ የኢንስፔክሽን ተግባራት በሀገር አቀፉ የኢንስፔክሽን ማዕቀፍና መመሪያ መሠረት ተግባራዊ መደረጋቸውን ይከታተላል፤

11.2.6. ከዞን/ ክፍለ ከተማ ትምህርት መምሪያና ከወረዳ ትምህርት ፅ/ቤት በየወሩ እየተዘጋጁ የሚቀርቡ የኢንስፔክሽን ሪፖርቶች ተገቢነትና የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ ስለመሆናቸው ያረጋግጣል፤

11.2.7. ከሁሉም ዞን/ክፍለ ከተማ ኢንስፔክሽን ዘርፍ የሚላኩ ሪፖርቶችን በማጠናቀርና በመተንተን የኢንስፔክሽን ተግባር ያስገኘውን ጥቅም ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፡፡

11.2.8. መልካም ተሞክሮዎች በመቀመርና በመለየት እንዲስፋፋ ያደርጋል፡፡

11.2.9. የኢንስፔክሽን መረጃ ይሰብስባል፣ ያደራጃል፣ ይተነትናል፣ ጥቅም ላይ ያውላል፤ ወቅታዊነቱን ይጠብቃል፡፡

11.2.10. በትምህርት ጥራት ማረጋገጥ ተግባር ዙሪያ ጥናትና ምርምር ያከናውናል፡፡

## 11.3 የዞን/ክፍለከተማትምህርትመምሪያኢንስፔክሽንዘርፍ፡-

11.3.1 በዞኑ/በክፍለከተማውውስጥበሚገኙየትምህርትተቋማትየኢንስፔክሽንሥራየማከናወንሃላፊነትአለበት፡፡

11.3.2 በተመሳሳይሁኔታከክልሉበተላከውሀገርአቀፍየኢንስፔክሽንማዕቀፍናመመሪያመሠረትበወረዳደረጃየትምህርትኢንስፔክሽንሥራስለመከናወኑክትትልናድጋፍያደርጋል፡፡

11.3.3 ከክልሉጋርበተደረገስምምነትበተዘጋጀውአመታዊየኢንስፔክሽንፕሮግራምመሰረትኢንስፔክሽንመካሄዱንያረጋግጣል፡፡

11.3.4 ወቅታዊየኢንስፔክሽንሪፖርቶችንበየወሩበቋሚነትለክልልትምህርትቢሮኢንስፔክሽንዘርፍይልካል፡፡

11.3.5 በወረዳዎችየሚከናወኑየኢንስፔክሽንስራዎችጥራታቸውንጠብቀውእንዲከናወኑድጋፍናክትትልያደርጋል፤

11.3.6 በኢንስፔክተሮችአማካኝነትየሚሰጡየማሻሻያሃሳቦችሥራላይእንዲውሉበወረዳዎችበኩልክትትልየሚደረግስለመሆኑይከታተላል፣ድጋፍያደርጋል፡፡

11.3.7 ከሁሉም ወረዳዎችኢንስፔክሽንዘርፍበየወሩተዘጋጅተውየሚላኩሪፖርቶችንበማጠናቀርና በመተንተንየኢንስፔክሽንተግባርያስገኘውንጥቅምለሚመለከተውአካልያቀርባል፡፡

11.3.8 መልካምተሞክሮዎችበመቀመርናበመለየትእንዲስፋፉያደርጋል፡፡

11.3.9 የኢንስፔክሽንመረጃይሰብስባል፣ያደራጃል፣ይተነትናል፣ጥቅምላይያውላል፤ወቅታዊነቱንይጠብቃል፡፡

11.3.10 በትምህርትጥራትማረጋገጥተግባርዙሪያጥናትናምርምርያከናውናል፡፡

## 11.4 የወረዳትምህርትጽ/ቤትኢንስፔክሽንዘርፍ፡-

11.4.1 ወረዳውለሁሉምአማራጭመሰረታዊትምህርትማዕከላት፣አፀደህፃናየመጀመሪያደረጃእንዲሁምእንደክልሉተጨባጭሁኔታለ2ኛደረጃትምህርትቤቶችየኢንስፔክሽንአገልግሎትየመስጠትሃላፊነትአለበት፡፡

11.4.2 ከክልሉተጨባጭሁኔታበመነሳትበዞን/ክፍለከተማደረጃበሚደረግአመታዊየኢንስፔክሽንተግባርዕቅድመሠረትሃላፊነቱንይወጣል፡፡

11.4.3 በሀገርአቀፉየኢንስፔክሽንማዕቀፍናመመሪያመሠረትበትምህርትተቋማትኢንስፔክሽንበማከናወንወርሃዊሪፖርትለዞን/ክፍለከተማየኢንስፔክሽንዘርፍይልካል፤ለሚመለከተውአካልያሳውቃል፡፡

11.4.4 የኢንስፔክሽንባለሙያዎችለትምህርትቤቱመሻሻልየሚሰጧቸውአስተያየቶችንተግባራዊለማድረግየጉድኝትማዕከሉሱፐርቫይዘሮችናየትምህርትቤቶችአመራሮችበአግባቡመፈፀማቸውንክትትልያደርጋል፣ይቆጣጠራል፡፡

11.4.5 መልካምተሞክሮዎችበመቀመርናበመለየትእንዲስፋፉያደርጋል፡፡

11.4.6 የኢንስፔክሽንመረጃይሰብስባል፣ያደራጃል፣ይተነትናል፣ጥቅምላይያውላል፤ወቅታዊነቱንይጠብቃል፡፡

11.4.7 በትምህርትጥራትማረጋገጥተግባርዙሪያጥናትናምርምርያከናውናል፡፡

## 11.5 ትምህርትቤቶች፡-

11.5.1 የራሳቸውንግለ-ግምገማናየት/ቤታቸውንደረጃምደባበትምህርትዓመቱመጨረሻወይምመጀመሪያያከናውናሉ፡፡

11.5.2 በየደረጃውየትምህርትቤቱንየትምህርትጥራትለማሻሻልናለማረጋገጥወደተቋሙከሚመጡባለሙያዎችጋርይተባበራሉ፤አስፈላጊውንመረጃየመስጠትናምቹሁኔታየመፍጠርሃላፊነትአለባቸው፡፡

11.5.3 በኢንስፔክሽንባለሙያዎችለትምህርትቤቱመሻሻልሲባልየተሰጡትንአስተያየቶችበሥራላይያውላሉ፣

11.5.4 የተማሪዎችመማርናውጤትጥራቱንጠብቆእንዲሰጥያደርጋሉ፡፡

11.5.5 በትምህርትጥራትማረጋገጥዙሪያየተግባርጥናትናምርምርያከናውናል፡፡

# 12 የኢንስፔክተሮችሙያዊፕሮፋይል

12.1 የትምህርት ኢንስፔክተሮች በፌዴራል፣ በክልል ፣ ከተማ አስተዳደር፣ በዞን፣ በክፍለ ከተማ እና በወረዳ በተቋቋሙ የአጠቃላይ ትምህርት ኢንስፔክሽን ዘርፎች ተመድበው የሚሠሩ ናቸው፡፡ ባለሙያዎቹ ከሚያከናውኗቸው ተግባራት መካከል ትምህርት ቤቶች ያሉባቸውን ጠንካራና ደካማ ጐኖች በመለየት አስፈላጊውን ግብረ-መልስ በመስጠት የትምህርት ጥራትንና የተማሪዎችን ውጤት ማሻሻል በዋናነት የሚጠቀስ ነው፡፡ በመሆኑም ይህንን ከፍተኛ ሃላፊነት በሚጠይቅ ስራ ላይ የሚመደቡት የትምህርት ኢንስፔክተሮች ምልመላና ስምሪት በጥንቃቄ መከናወን የሚገባው ተግባር ነው፡፡

ስለሆነም በየደረጃው ባሉ የትምህርት አስተዳደር እርከኖች የሚመደቡት የትምህርት ኢንስፔክተሮች ምርጫ በሚከተሉት መስፈርቶች መከናወን ይኖርበታል፡፡

ሀ/ በማንኛውም የትምህርት መስክ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው/ያላት፣

ለ/ በመምህርነት ወይም በርዕሰ መምህርነት፣ በትምህርት ሱፐርቫይዘርነት ወይም በትምህርት አመራርቢያንስ አምስት ዓመት የሥራ ልምድ ያለው/ያላት፣

ሐ/ በመምህርነት ወይም በርዕሰ መምህርነት፣ በሱፐርቫይዘርነት ወይም በትምህርት አመራር የላቀ የሥራአፈፃፀም ያለው/ያላት፣

መ/ መልካም ሥነ-ምግባር ያለው/ያላት፣

ሠ/ ቢቻል በትምህርት ኢንስፔክሽን የስልጠና ኮርሶች ላይ የተሣተፈ/የተሣተፈች ቢሆን/ብትሆን ይመረጣል፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ የትምህርት ኢንስፔክተሮች በሙያቸው የላቀ እውቀትና ክህሎት እንዳላቸው በምልመላው ወቅት መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ከነዚህም መካከል የሚከተሉት በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

ረ/ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ፣ ልዩ ልዩ የትምህርት ስትራቴጂዎችና መመሪያዎች ላይ በቂ ግንዛቤ ያላቸው፣

ሰ/ በትምህርት ቤት መሻሻል መርሃ-ግብር ላይ ከፍተኛ እውቀትና ግንዛቤ ያላቸው፣

ሸ/ በሃገሪቱ በስራ ላይ ባሉ የሥርዓተ ትምህርት ቁልፍ መሣሪያዎች (የአጠቃላይ ትምህርት ስርዓተ ትምርት ማዕቀፍ፣መርሃ ትምህርት፣ዝቅተኛ ተፈላጊ የችሎታ

መለኪያ(MLC)፣የይዘት ፍሰት/content flowchart/፣ ወዘተ) ላይ የላቀ እውቀት ሊኖራቸው ይገባል፣

ቀ/ በአሁኑ ወቅት ስላለው ሀገራዊና አለም አቀፋዊ የትምህርት ትኩረት አቅጣጫዎች በቂ እውቀት ያላቸው፣

በ/ ፕሮጀክቶችን የመምራት ልምድ ያላቸው ፣

ተ/ ልዩ ልዩ መረጃዎችን ማሰባሰብ፣ ማደራጀት፣ መተንተን፣ማጠናቀርና ማሠራጨት የሚችሉ ፣

ቸ/ አጠቃላይ ሪፖርት የማዘጋጀት ችሎታና ብቃት ሊኖራቸው ይገባል፣

ነ/ መሠረታዊ የኮምፒውተር እውቀት ያላቸው፣

ከላይ የተጠቀሱት የመመልመያ መስፈርቶች እንደየክልሉ ተጨባጭ ሁኔታና በተጠና የሲቪል ሰርቪስ መመሪያና ደንብ መሠረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

# 13 የኢንስፔክተሮችሙያዊስነ-ምግባር

ማንኛውምኢንስፔክተር፡-

13.1. በትምህርት ተቋማት ውስጥ ለሚያከናውናቸው/ለምታከናውናቸው ተግባራት ሙያዊ አቀራረብ እንዲኖረው/እንዲኖራት ይጠበቃል። ኢንስፔክተሩ/ሯ ከትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ጋር የሚያደርጋቸው/ የምታደርጋቸው ውይይቶችና ግንኙነቶች በመከባበር ላይ የተመሰረቱ ሊሆን ይገባል፣

13.2. አንድ ኢንስፔክተር በተቻለ መጠን የትምህርት ቤቱን መማር ማስተማር ሳያስተጓጉል/ሳታስተጓጉል ስራውን ለማከናወን ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል/ባታል፤

13.3. በሀገር አቀፉ የኢንስፔክሽን ማዕቀፍና መመሪያ መሠረት ሥራውን ያከናውናል/ ታከናውናለች፣

13.4. በኢንስፔክተሩ/ሯ የሚወሰኑ ውሳኔዎች በተጨባጭ መረጃ ፣ ሚዛናዊነትና ፍትሃዊነትን በጠበቀ መልኩና ግልፅነት በተሞላበት ሁኔታ መከናወን ይኖርባቸዋል፣

13.5. ከትምህርት ቤቱ ጋር የሚደረግ ውይይት ት/ቤቱን የሚገነባ፣ ውጤትን ሊያመጣ የሚችል እንጂ ስህተት ፈላጊ መሆን የለበትም፡፡ በአጠቃላይ የትምህርት ቤቱን የወደፊት መሻሻል የሚያሳይ መሆን ይኖርበታል፣

13.6. የተማሪዎችን ውጤታማነት ለማሻሻል አስተያየቶች የሚኖራቸው አተዋጽኦ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውንም በስራ አጋጣሚ የተሰበሰበ መረጃ ሚስጥራዊነት የመጠበቅ ሃላፊነትና ግዴታ አለበት፡፡

13.7. ኢንስፔክተሮች ገለልተኛና ውጫዊ አካል በመሆን በተጨባጭ መረጃዎች ላይተመስርተው አስፈላጊ መረጃዎችን በማሰባሰብ የውሳኔ ሀሳቦችን ያቀርባሉ፡፡

## ክፍልአራት

## ልዩ ልዩ ሁኔታዎች

## 14 የቅሬታአቀራረብናየውሳኔአሰጣጥ፡-

14.1 በኢንስፔክሽንሥራወቅትአንድትምህርትቤትበአግባቡአልታየሁምብሎቅሬታካ ደረበትበጽሁፍውሳኔበተሰጠውበ5/አምስት/ቀናትውስጥበቅርብለሚመለከተውየ ወረዳ/ የዞን/ የክልል/ የከተማትምህርትጽ/ቤት/ቢሮኢንስፔክሽንዘርፍቅሬታውንማቅረብይችላል፡፡

14.2 ቅሬታውንየተቀበለውየኢንስፔክሽንዘርፍከ15/ አስራአምስት/ቀናትባልበለጠጊዜውስጥተገቢውንመልስለአቤቱታአቅራቢውተቋ ምማሳወቅአለበት፡፡

14.3 ቅሬታየቀረበበትየኢንስፔክሽንዘርፍየሰጠውመልስካላረካውወዲያውኑለአቀረበበ ትዘርፍየበላይኃላፊቅሬታውንማቅረብይችላል፡፡

14.4 የመ/ቤቱየበላይኃላፊቅሬታውበቀረበ 5/በአምስት/ቀናትውስጥመልስመስጠትአለበት፡፡

14.5 ቅሬታአቅራቢውአሁንምበተሰጠውውሳኔካልረካለሚቀጥለውየትምህርትዘርፍየበ ላይአካልበማቅረብእንዲታይናውሳኔእንዲሰጠውበማድረግየመጨረሻውውሳኔይ ሆናል፡፡

## 15 በመመሪያውያልተሸፈኑጉዳዮች

በዚህ መመሪያ ውስጥ ያልተሸፈኑ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ የክልሉ/ከተማ/ዞን/ወረዳ ትምህርት ኢንስፔክሽን ዘርፍ በኩል እየቀረቡ እንደ አስፈላጊነቱ ውሳኔ የሚሰጣቸው ይሆናል፡፡

## 16 መመሪያውንስለማሻሻል

ይህ መመሪያ ተግባር ላይ ውሎ በሚቀርቡ የማሻሻያ ሃሳቦችና የዳሰሳ ጥናቶች መሠረት በትምህርት ሚኒስቴር ሊሻሻልይችላል፡፡

## 17 የተፈጻሚነትጊዜ

ይህ መመሪያ ከ—— ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡